# መመርያዎች



## በኣካል ሳይገኙ እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ

**የሚያስፈልጉት ነገሮች**

- የምርጫ ካርድ*
- ቡናዊ ቀለም ያለው ፖስታ*
- ለመምረጥ የተመዘገቡበት ማመልከቻ*
- ነጭ የሲግኔቸር ፖስታ(signature envelope)*
- ተለቅ ያለ ነጭ የመመለሻ ፖስታ*
- ጥቁር ቀለም ያለው ብዕር
- የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድ ወይም ማናቸውም የት እንደሚኖሩ ኣድራሻዎን የሚያሳይ ህጋዊ ማረጋገጫ *ለሌሎች ኣማራጮች በስተጀርባ ይመልከቱ*

* ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ኣንድ ቢጎድል፡ የቀበሌዎን የምርጫ ባለስልጣንን ያነጋግሩ

- የመታወቅያ ወረቀትዎ ቁጥር
  የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድዎ ቁጥር የሚኖሶታ መታወቅያ ወረቀት ቁጥር ወይም የሶሻል ሴኩሪቲ ወረቀትዎ የመጨረሻዎቹ ኣራት ቁጥሮች
  *ከእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኣንዱም ከሌሎት ከታች ተመልከቱ*
- ምስክር
  *ማንኛውም በሚኖሶታ ለመምረጥ የተመዘገበ ሰው፡ ባለቤትዎ ወይም ዘመድዎ ጭምር ሊሆኑ ይችላሉ*
  ወይም የታወቀ ህጋዊ ሰው ወይም ማህላ ለማስፈጸም ህጋዊነት የተሰጠው ሰው

ኣስፈላጊ፡ የሰጡት ድምጽ እንዲቆጠር ፡ ለመምረጥ መዝገቡኝ ብለው ያቀረቡትን ማመልከቻን ከምርጫ ካርዱ ጋር፡ በነጩ ፖስታ ውስጥ ኣሽገው መላክ ኣለብዎ።




### ❶ የምርጫ መመዝገብያ ማመልከቻውን ሞልተው ፊርማዎን ኣስፍሩበት።

- ለምስክሮ የመንጃ ፍቃድዎን ወይም የት እንደሚኖሩ የሚያረጋግጡ ሌሎች ማስረጃዎች ካሎት ኣሳዩት።
  *በስተጀርባ የሚገኙትን ሌሎች ኣማራጮችን ተመልከቱ*




### ❷ ድምጽን ይስጡ/ምረጡ!

- ባዶ የምርጫ ወረቀትዎን ለምስክሮቹ ካሳዩ በውሃላ ለብቻዎ ሁነው ምርጫዎ ላይ ምልክት ያድርጉ
- በምርጫ ወረቀቱ ላይ ያሉትን መመርያዎች ተከተሉ
- በምርጫው ወረቀት ላይ ስሞንም ሆነ የመታወቅያ ወረቀት ቁጥሮን በምንም ቦታ ላይ ኣይጻፉ
- ከተፈቀደው ቁጥር በላይ ዕጩዎችን ኣትምረጡ። ይህንን ካደረጉ በዛ ምርጫ ጣብያ ውስጥ የሰጡት ድምጽ ተቀባይነት ኣያገኝም። *በምርጫ ወረቀትዎ ላይ ስህተት ካረጉ ፡ ከምርጫ ወረቀቱ በስተጀርባ ተመልከቱ።*




### ❸ የምርጫ ወረቀትዎን ቡናዊ ቀለም ባለው ፖስታ ውስጥ ከተው ያሽጉት።

- በዚህ ፖስታ ላይ ምንም ነገር ኣይጻፉ

### ❹ ቡናዊ ቀለም ያለውን የምርጫ ወረቀትዎን የያዘውን ፖስታና ለመምረጥ የተመዘገቡበትን ማማልከቻ ኣጠቃለው በነጩ ሲግኔቸርፖስታ ውስጥ ይከተቱ።




### ❺ ነጩን የስግኔቸር ፖስታ ሙሉ በሙሉ ይምሉት።

- ምልክት ከሌለው፡ ስሞንና የሚኖሶታ ኣድራሻዎን ይጻፉ።
- የሚኖሶታ የመንጃ ፈቃድዎን ቁጥር፡የሚኖሶታ መታወቅያ ወረቀትዎን ቁጥር፡ ወይም የሶሻል ሴኩሪቲ ካርዶን የመጨረሻዎቹን ኣራት ቁጥሮች ይጻፉ።
  እነኚህ ያስገብዋቸው ቁጥሮች፡ በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከቀኑ በፊት ለሚመርጡ የሚሰጥ የምርጫ ወረቀት እንዲሰጥዎ ባስገቡት ማመልከቻ ላይ ያሰፈሩዋቸው ቁጥሮች ጋር ኣንድ ዓይነት መሆናቸውን ያረጋግጡ ።
  *እነዚህ ቁጥሮች ከሌሎት፡ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።*
- ቃለ መሃላውን ኣንብበው ይፈርሙ።
- ምስክርዎ ስማቸውን እንዲያሰፍሩ፡ የሚኖሶታ የከተማ ኣድራሻቸውን እንዲሁም የሚኖሩበትን ከተማ ( የፖ.ሳ.ቁ. ሳይሆን) በዝርዝር እንዲጽፉ፡ የትኛውን መረጃ ከእርስዎ እንዳገኙ እንዲያመለክቱ በመጨረሻም እንዲፈርሙ ይጠይቁ።
  *ምስክር ባለስልጣን ወይም የታወቀ ህጋዊ ኣካል ከሆነ፡ ከኣድራሻ ይልቅ ስልጣናቸውን ማስፈር ኣለባቸው። በህግ የታወቀ ኣካል ከሆነ ደግሞ ማህተማቸውን ማስፈር ኣለባቸው።*
- *ፖስታውን ያሽጉ።*




### ❻ የግሎ መረጃዎች ሁሉ እንዳይታዩ፡ የሲግኔቸር ፓስታውን በትልቁ የመመለሽያ ነጭ ፖስታ ውስጥ ይከተቱ።

- *ፖስታውን ያሽጉ።*




### ❼ የምርጫ ወረቀትዎን፡ በመመለሻው ፖስታ ላይ ወደ ተጻፈው ኣድራሻ፡ ምርጫ በሚካሄድበት ቀን እንዲደርስ ይላኩ ። የምርጫ ወረቀትዎ ወደ ምርጫ ጣብያው ላይደርስ ይችላል።

ይህ እንዳይሆን ሶስት ኣማራጮች ኣሎት፡

- ወረቀትዎ ምርጫ በሚካሄድበት ዕለት እንዲደርስልዎ፡ በዩ ኤስ ፖስታቤት ወይም ኣቃ በሚያግዙ ኣገልግሎቶች ይላኩ።
- የምርጫ ቀን ከመድረሱ በፊት በኣካል ሂደው ይስጡ ወይም በምርጫው ዕለት ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት በፊት ይስጡ።
- ሌላ ሰው፡ በምርጫው ዕለት ከዘጠኝ ሰዓት በፊር ሂዶ እንዲሰጥሎት ይጠይቁ።
  *ይህ ሰው ከሶስት የምርጫ ወረቀቶች በላይ ሊያስረክብ ኣይችልም።*




የዚህ በኣካል ሳይገኙ ያካሄዱት የምርጫ ውጤት ምን እንደሆነ ለማየት **www.mnvotes.org**ን ይጎብኙ።

## የት እንደሚኖሩ የሚያረጋግጡ አማራጮች

ወቅታዊ የሆነ የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድ፡ የሚኖሶታ መታወቅያ ወረቀት፡ ወይም ወቅታዊ የሆነ የመኖርያ ቤትዎን አድራሻ የሚያሳይ የፍቃድ ወረቀት ወይም

ፎቶግራፎ ያለበት ግን አድራሻዎ የሌለበት የመታወቅያ ወረቀት፡ አድራሻዎ ካለበት ሊላ ወረቀት ማስታከክ

- ህጋዊ የሆነ ፎቶግራፎ ያለበት መታወቅያ ወረቀት፡ የሚኖሶታ ወይም የሌላ ክፍለሃገር የመንጃ ፍቃድ፡ መንጃ ፍቃድ፡ ወይም የመታወቅያ ወረቀት፡ የኣሜሪካን ፓስፖርት፡ የኣሜሪካን ሚሊታሪ ወይም የኣሜሪካን የቀድሞ ወታደሮች የመታወቅያ ወረቀት የሚኖሶታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ መታወቅያ ወረቀት ወይም በህንዶች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት (BIA-ቢ-ኣይ-ኤ) ተቀባይነት ያለው፡ ፊርማዎ ያለበት የጎሳዎ መታወቅያ ወረቀት።
- ወቅታዊ ኣድራሻዎ ያለባቸው ህጋዊ ዶኩመንቶች፡ ግልባጭ ያልሆነ የሂሳብ ደረሰኝ፡ ምርጫው በሚካሄድበት 30 ቀናት ውስጥ የሚከፈል ፡ ወይም ከምርጫው በፊት ወይም በውሃላ እንዲከፈል የተላከ የክፍያ ወረቀት፡ ባንክ ውስጥ ያለ የገንዘብ ሂሳብ፡ ማናቸውም ኣገልግሎት መቀበል የጀመሩበትን ድረስ የሚቀጥል ቤት የተከራዩበት የኪራይ ስምምነት። ህጋዊ ክፍያዎች ተብለው የሚጠሩት፡ የጋዝ፡ የኤሌክትሪክ፡ የቁሻሻ መጣያ፡ የውሃ፡ የመጸዳጃ ቤት ጉድፍ መጣያ፡የቤት ስልክ፡ የእጅ ስልክ፡የቴሌቪዥን፡ የኢንተርኔት ኣገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፡ የባንክ ብድር ወረቀት(ክሬዲት ካርድ) የባንክ ኣገልግሎት፡ የቤት ኪራይ፡ ወይም ቤት የገዙበት ክፍያዎችን ያጠቃልላል።

ወይም ደግሞ ከሚከተሉት ውስጥ ኣንዱ

- ወቅታዊ ኣድራሻዎ ያለበት የሚኖሶታ ህጋዊ የመንጃ ፍቃድ፡ የሚኖሶታ መታወቅያ ወረቀት፡ ወይም ግዚያዊ የመንጃ ፈቃድ ያለበት ቢጫ ህጋዊ ደረሰኝ።
- ዋስትና፡ በኣካባቢዎ የሚኖር፡ በግል የሚያውቆትና በዛ ኣካባቢ እንደሚኖሩ የሚያረጋገጥ፡ ለመምረጥ የተመዘገበ ሰው ፊርማ ይሄው ምስክሮ ለመምረጥ በዛው ኣካባቢ የተመዘገበ ከሆነ ስለእርስዎ ሊመስክርልዎ ይችላል።
  ይህ ሰው፡ በምርጫው መመዝገብያ ማመልከቻ በስተጀርባ ላይ መፈረምና ፎርሙን ሞልቶ ማጠናቀቅ ኣለበት።
- ስምዎ፡ ኣድራሻዎ፡ ፊርማዎ, ስዕሎ ያለበት በ ቢ-ኣይ-ኤ የታወቀ የጎሳዎ መታወቅያ ወረቀት።
- “ዘግይተው የተመዘገቡ” የሚል ጽሁፍ ከኣውራጃው ተቆጣጣሪ ክፍል ወይም ከከተማው ጸሃፊ ያሎት ከሆነ።
- በሚኖሩበት ኣካባቢ ወደ ሌላ ቤት ከቀየሩ ወይም ስሞን ከቀየሩ በኣካባቢው የተመዘገብቡበት ወረቀት።
- በተወሰኑ የመኖርያ ኣካባቢዎች ለሚኖሩ ተቀማጮች የሚሰጥ ዋስትና፡ በምታስተዳድሩዋቸው ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ፊርማ፡ እነዚህ ቤቶች - የማስታመምያ ቢቶች(ነርሲንግ ሆምስ)፡ የጋራ ቤቶች(ግሩፕ ሆምስ) ፡ ጉዳት የደረሰባቸው ሰኢቶች መጠግያ ቤቶች( ባተርድ ዊሜንስ ሽልተርስ)፡ መኖርያ የሌላቸው ሰዎች መጠግያ ቤቶች( ሆምለስ ሆምስ) የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። የሚኖሩበት ቤት በዚህ ውስጥ መጠቃለሉንና ኣለመጠቃለሉን ለማወቅ ከፈለጉ ወደ ቀበሌ ኣስመራጭ ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ይደውሉ።
  ሰራተኛው፡ በመርጫ መመዝገብያ ማመልከቻ በስተጀርባ የሚገኘውን የዋስትና ሰጪ ወረቀት መሙላትና መፈረም ኣለበት።

---

## ስህተተን ማረም




- በቂ ግዜ ካሎት፡ የምርጫ ኮሚቴው ኣዲስ የምርጫ ወረቀት እንዲልክሎ ይጠይቁ ወይም።
- በስህተት ምልክት ያደረጉበትን የዕጩውን ስም በደንብ ኣድርገው ይሰርዙት። ከዛ በውሃላ በሚመርጡት ሰው ስም ላይ ምልክት ያድርጉ። (ባደረጉት እርማት ላይ የስሞን ኣህጽረ- ቃል ኣታስፍሩ)።

---

## የኣካል ጉድለት ካለቦ

የኣካል ጉድለት ካለቦ ወይም ምርጫዎ ላይ ምልክት ለማድረግ የማይችሉ ከሆነ፡ ምስክሮ፡ እርስዎ በሚሰጡት መመርያ መሰረት ምርጫዎ ላይ ምልክት በማድረግ፡ ማንኛውንም ነገሮች በማሰባሰብና ፎርሞችን በመሙላት ሊተባበርዎ ይችላል።

በምርጫው ፖስታ ላይ ሲፈርሙ፡ የሚኖሶታ ህግ እንደሚከተለው ማድረግ ኣለቦት ይላል፡

- ወደ ምርጫ ጣብያ የሚላከውን ወረቀት መፈረም ያለቦት ራስዎ ኖት ወይም
- ምልክት ማድረግ ያለቦት ራስዎ ኖት ወይም
- እርስዎ ራስዎ ባሉበት፡ ምስክሮ እንዲፈርምልዎ መጠየቅ ይችላሉ (ምስክሩ የራሱንም ስም ጭምር መፈረም ኣለበት)።
- ፊርማዎ ያለበት ማህተም ካሎት ፡ እሱን መጠቀም ይችላሉ ወይም ምስክሮን እርስዎ ባሉበት ማህተሞን ተጠቅሞ ፊርማዎን እንዲያስቀምጥሎት ይጠይቁ።

የሚኖሶታ ህገ-መንግስት፡ ክፍል 645.44፡ ክፍል 14

በደንብ ይመልከቱ፡ በውክልና ድምጽ መስጠት ኣይቻልም። ከላይ እንደተጠቀሰው፡ ውክልና የተሰጠው ሰው፡ በእርስዎ ፊት ሊፈርምልዎ ብቻ ነው የሚችለው።

---

የሚስጥራዊነት ማስታወቅያ፡ የምርጫ ወረቀትዎ ተቀባይነት ካገኘ፡ ስሞና ኣድራሻዎ፡ ምርጫንና ፖለቲካን በሚመለከት፡ ለህጋዊ ጉዳዮች ጠቀሜታ ለህዝብ ክፍት ይሆና። ከዚህ በስተቀረ፡ በምርጫ ወረቀትዎ ላይ ያስቀመጡት መረጃ ሁሉ ለኣስመራጭ ኮሚቴው ባለስልጣኖች ብቻ በምርጫው ቀን እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ብቻ ክፍት ሆኖ ይቆያል። ከዛ በውሃላ የምርጫው ወረቀትዎና በላዩ ላይ ያለው መረጃ ሁሉ(ከመታወቅያ ወረቀት ቁጥሮ በስተቀር) ለህዝብ ክፍት ይሆናል።የመታወቅያ ወረቀትዎ ቁጥር የሚያስፈልግበት ምክንያት በኣካል ተገኝቼ ለመምረጥ ኣልችልምና የምርጫ ወረቀት ላኩልኝ ብሎ ማማልከቻ ያስገባው ሰው እርስዎ መሆንዎንና ኣለመሆኖን ለማረጋገጥ ነው። ኣልሰጥም ለማለት ይችላሉ። ግን የምርጫ ወረቀትዎ ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል። በተጨማሪም የምርጫ ወረቀትዎ ምን ላይ እንደደረሰ ከመከታተል ይታገዳሉ ማለት ነው።